የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

*Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

ታህሣሥ 11 ቀን 2003 ዓ.ም

## የቀይ ሽብርና የሕዝብ ፍጅት ወንጀለኞች ይፈታሉ የተባለውን በተመለከተ መግለጫ

## ወያኔያዊ ምህረት ለገዳዮች

ፍትሕ አልባ ሀገራችን ነጋ ጠባ ገፍና ጉድን እያመጣች መገረም አበቃን ስንል ይበልጥ ጉድ እያሰኘችን አለች፡፡ የቀይ ሽብር ወንጀሎቅች ከታሰሩበት በጅምላ ሊፈቱ ነው የሚለው ዜና መች ይሆን ሕዝባችን ፍትህን የሚያገኘው ብለን እንድናማርር አስገድዶናል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን፣ የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርሰቲያንና የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርሰቲያን መካነ ኢየሱስ በጋራ ለሕዝብ ባወጡት መግለጫ በእስር ቤት ያሉት የቀድሞው አረመኔ አገዛዝ ባለሥልጣናት – እነ መላኩ ተፈራ፣ ተስፋዬ ወልደ ሥላሴና ቀልቤሳ ዓይነት አውሬዎች፣ ...ወዘተ በ "ጥፋታቸው ተፀፅተው ይቅር በሉን ብለዋልና" እንዲፈቱ እየጣርን ነው ብለዋል፡፡ በመጪው ገና በዓል ጊዜም ይፈቱ ይሆናል የሚል ዜናን ለአገዛዙ ቅርበት ያላቸው ጋዜጦችም ዘግበዋል፡፡ ይህን በተመለከተ ኢሕአፓ በጥብቅ ተቃውሞውን እያሰማ ከሀዲውን የወያኔ አገዛዘንም ያወግዛል፡፡

አራቱም የሃይማኖት ተቋሞች፣ መሪዎች ባለፉት 19 ዓመታት አንድ ጊዜም ሕዝብ ተበደለ፣ ተገደለ፣ ለስየልና እስራት ተዳረገ፣ በአደባባይ በየቦታው ፍጅት ተፈፀመበት ብለው በለሆሳስ እንኳን ተቃውሞ ሲያሰሙ ለመስማት ሳንታደል ቆይተን አሁን የወያኔን ፖለቲካ ለማራመድ ወንጀለኞችን ልናስለቅቅ እነሆ ስንጥር ሁለት ዓመት አለፈንና ጥረታችንን መርቁልን ማለታቸው ምንኛ ለእምነታቸው እንኳን የማይቆሙ መሆናቸውን የሚያረጋግጥልን መሆኑን መጥቀስ እንፈልጋለን፡፡ ኃጢያት፣ ሀራም፤ እንላቸዋለን፡፡ ዛሬ መላ ሀገሪቷ እስር ቤት ሆና፤ ብዙዎች ደብዛቸው ጠፍቶ፤ እዚያው አዲስ አበባ ራሱ ውስጥ በምስጢር እስር ቤቶች ስንቱ እየተሰቃየ ፤ በግንቦት 97 የታሰሩ ስንቶች ዛሬም ደብዛቸው ጠፍቶ እያለ ፤ የኢሕአፓና የሌሎች ድርጅቶች አባል፣ ደጋፊ፣ ...ወዘተ ተብለው ስንቶቹ ታግተው ባሉበት ለነዚህ ቅንጣትም የመቆርቆር ስሜት ያላሳዩት የሃይማኖት መሪዎች የሕዝብ ደም ያፈሰሱትን ይለቀቁልን ብለው መፀለያቸው ሀሳውያን እንጂ ሌላ አያደርጋቸወም፡፡

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

ቀይ ሽብርን በተመለከተ ወያኔ ራሱ በአቅሙ በትግራይ የተካፈለበት ግፍ ሲሆን ከዚህ ቀደም ደግመን ደጋግመን ገልፀን እንደነበረው ወያኔ የቀይ ሽብር ወንጀለኞች ላይ ዳኛ ለመሆን ብቃቱም ፍላጎቱም ሆነ ሕጋዊነቱም የለውም፡፡ ወንጀለኞቹን መቅጣት ሆነ መማር የሚችለው ሕዝብ ብቻ ነው፡፡ የስንት መቶ ሺ ሰማዕት ዜጋ ጓዶችና ወላጆች፣ ዘመዶች ብቻ ናቸው ሊፋረዱም ሊምሩም የሚችሉት፡፡ ወያኔ የቀይ ሽብር አራማጅ አገዛዝን ሲታገሉ የቆዩትን ለእስርና ስቃይ ዳርጎ ያለ አገዛዝ ሲሆን፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲሉ ጨቋኝ አገዛዞችን የታገሉትንም ለእስርና ስደት ዳርጎ ጨቋኝ ገዢዎቹንና ርዝራዦቻቸውን ግን ነፃ ሲለቅና ባለመብትም ሲያደርግ እያየን ነው፡፡ ሕዝብን መናቅና መበደል ይሏል ይህ ነው--የግፍ ላይ ግፍ! እነፀጋዬ ገብረ መድህንና ጓዶቹ ታስረው እነመላኩ ተፈራና ቀልቤሳ ዓይነቶቹ ነፃ ሲወጡ እንድናይ ሊደረግ መሆኑ መቸም በሀገርና በሕዝብ መሳለቅ መሆኑ ቤተ መንግሥት ላሉት አረመኔዎች ጠፍቷቸው አይደለም፡፡ በሕዝብ ደም ላይ ሲቀልዱ እንጂ ነው!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ደሙን ያፈሰሱትን ሁሉ ይፋረዳል!!
ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች በአስቸኳይ ይፈቱ!!
የወያኔ አገዛዝም ይወድማል!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France